በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሴፕቴምበር 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከሴፕቴምበር 11-20 እና ከሴፕቴምበር 21-30 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ከሴፕቴምበር 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........................................- 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች- 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.............- 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት.........................- 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........................................- 3 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1 እስከ 10 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........................................- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ......................- 5 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........................................- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ......................- 6 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ........................................- 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........................- 8 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ........................................- 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ..........................- 9 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........................................- 9 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........................................- 10 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


### እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት ቀናት ለዝናብ መፈጠርና መስፋፋት አተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ተጠናክረው በመጠናከራቸው ምክንያትበብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎችን ያዳረሰ የዝናብ ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተለይም በምስራቅ አማራ፣ በምዕራብ ትግራይና ኦሮሚያ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ከተጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ዝናብ ነበራቸው፡፡ ባለፉት ቀናት ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአዲስ አበባ ቦሌ 32.2፣ በባህር ዳር 62.5፣ በኮምቦልቻ 47.0 እና 45.4፣ በጂማ 30.7፣ በአልጌ 40.0 እና 60.0፣ በአምደ ወርቅ 31.5 እና 44.0፣ በአንገር ጉቲን 30.4፣ በአርጆ 34.2፣ 41.2፣ 38.4 እና 34.2፣ በአርሲ ሮቤ 39.6፣ በአፅቢ 44.0፣ 40.2፣ በቡሬ 45.7 እና 60.3፣ በቻግኒ 31.8፣ በጨፋ 30.6፣ በጭራ 36.7፣ በደብረ ታቦር 31.1 እና 41.1፣ በዳንግላ 37.5 እና 32.0፣ በደብረ ወርቅ 86.6፣ በደምቢ ዶሎ 31.5፣ በፉኚዶ 35.0 እና 45.8፣ በጊዳ አያና 45.5፣ በጊምቢ 39.8፣ በሊሙ ገነት 45.2፣ በማሻ 30.5 እና 40.0፣ በሞጣ 48.6፣ በሻምቡ 42.6፣ በተርጫ 44.3፣ በሶዶ 32.6፣ በየትኖራ 34.5፣ በጨለንቆ 55.3፣ በቡለን 40.2 እንዲሁም በቢሾፍቱ 31.2ሚ.ሜ. የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት በ32 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-86.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በደብረ ወርቅ፤ በባህርዳር፤ በቡሬ፤ በአልጌ፤ በጨለንቆ፤ በሞጣ፤ በኮምቦልቻ፤ በፉኙዶ፤ በጊዳአያና፤ በሊሙገነት፤ በተርጫ፤ በአምደ ወርቅ፤ በአፅቢ፤ በሻምቡ፤ በአርጆ፤ በደብረ ታቦር፤ በቡለን እና በማሻ ይጠቀሳሉ (ምስል 1)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች


ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ የምስራቅ እና የምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ ወሎ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኙዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጉጂ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከሲዳማ ክልል ምዕራባዊው ክፍል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ እንዲሁም ከሶማሌ የዳዋ ዞን ላይ ከ 31-220 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከትግራይ የመካከለኛው፣ የምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአማራ ሰሜን ወሎ እና ዋግህምራ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ እና አውሲ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ እና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀላባ ዞን እንዲሁም ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ቡርጂ፣ ኮንሶ እና አማሮ ዞኖች ላይ ከ11-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1 እስከ 10 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋና ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም በመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንዲሁም በክረምት ወቅት ተዘርተው ፍሬ በማፍራትና በማበብ እንዲሁም በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉት የብዕር ሰብሎች፣ የጥራጥሬ እና የቅባት እህሎች ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታው የጎላ ነበር። በሌላ መልኩ ደረቅ ሁኔታ በነበራቸው የደቡብ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ በአሥሩ ቀናት ውስጥ ዝናብ በማግኘታቸው በአካባቢው ለሚካሂደው የእርሻ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የጎርፍ ክስተቶች፣ የመሬት አቀማመጣቸው ከፍተኛና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት፣ መሰንጠቅና ናዳ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መዋለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ በተለይም በሰሜን ሸዋ ዞን አሳግርት ወረዳ ከነበረዉ የመሬት መንሸራተት ጋር ተያይዞ በሰብሎች እና በንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ከተለያዩ የመስክ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል(ካርታ 4)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ መረብጋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፤ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ እና የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ በተለይም በመካከለኛው አባይና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ነበራቸው፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ በየተፋሰሶቹ በሚገኙ ግድቦች፣ ሰው ሰራሽ የውሃ መያዥያዎች እንዲሁም የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር ውሃ ሃብትን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ ተፋሰሶቸ ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የጎርፍ ክስተቶች ነበሩ፡፡ ከነዚህም በባሮ አኮቦ ተፋሰሰ በጋምቤላ ክልል በኑኤር ዞን የጎረፍ ክስተት የነበረ ሲሆን በሰዎች ላይም መፈናቀል አድርሷል (ካርታ 5) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚዳከሙ ሲሆንና፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በመጪዎቹ የሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ የሚሄድ ሲሆንና ከዚህ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከትግራይ ክልል የማዕከላዊ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ምዕራብ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርስ፤ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ አዲስ አበባ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ የቀበና፣ የጠምባሮ እና የማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ እንዲሁም የየም ልዩ ዞን፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 )፡፡

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና፣ ጉጂ ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ከአፋር ክልል ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና ጋቢ፣ ዞኖች፤ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ ዞኖች፤ ከትግራይ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ክልል ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ እና ወላይታ፣ ኮንሶ፣ አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ ከሁለተኛው ሳምንት ጀምሮ እየተዳከሙ ስለሚመጡ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭትም ይቀንሳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በደቡብ እና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሶስተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ የሚሄድ ሲሆንና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡

በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለፍራፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት መጠን ከማሟላት አንጻር ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል የእርጥበት ሁኔታው በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን አካባቢዎች የሚኖረው መስፋፋት የማሳ ዝግጅት ለማድረግና የበጋ ወቅት ሰብሎችን ለመዝራት እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም የገናሌዳዋ ተፋሰሶች ከከመጠናኛ እስከ ፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለገጸ ምድር እና ለከርሰ ምድር የውሃ ሀብት መጎልበት አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ወደ ግዶቦች የሚገባው ውሃ ከፍተኛ በመሆኑ በቀጣይ አስር ቀናትም አሁናዊ የውሃ ከፍታቸው አስጊ በሆነባቸው ማለትም ከአዋሽ ተፋሰስ የቆቃ፣ የከሰም እና የተንዳሆ ግድቦች፣ ከአባይ ተፋሰስ ደግሞ የጣናበለስ፣ የርብ እና የፊንጫ ግድቦች ከውሃ መብዛት ጋር የተያያዘ ጫና ሊኖራቸው እና በተለይም በተፋሰሱ የታችኛው አካባቢዎች ላይ ጉዳት እንዳያያከትል የቅርብ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et